በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ት/ፅ/ቤት የ2ኛ ወሰነ ትምህርት የ6ኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርት ሞዴል ፈተና

ሚያዚያ 2016ዓ.ም / April 2024GC

የጥያቄው ብዛት፡ 30 የተፈቀደው ሰዓት፡ 1ሰዓት

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ ሂሳብ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ለእያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኃል። መልስ የሚሰጠው ለብቻ በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር የሚመለስ ሲሆን የሚሰራው በእርሳስ ብቻ ነው፤ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።
መልስ የሚሰጠው በመልስ መስጫው ላይ ብቻ ነው፤ ለምሳሌ መልሳችሁ ለ ከሆነ ከታች በሚታየው መልክ ማጥቆር አለባችሁ።

ሀ ለ ሐ. መ.

@EtMathsNetwork

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ ተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያት የተጠቀማችሁበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለባችሁ። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችሁ ተቀምጣችሁ መጠበቅ አለባችሁ።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከበር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደርጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባቸውን መረጃዎች በሙሉ በጥንቃቄ መሙላት አለባችሁ።

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም!
መልካም ፈተና

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ት/ፅ/ቤት የ2ኛ ወሰነ ትምህርት የ6ኛ ክፍል የሒሳብ ትምህርት ሞዴል ፈተና

ሚያዚያ 2016ዓ.ም / April 2024GC

1. **ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል ተጋማሽ የሆነው የቱ ነው?**

   ሀ. 345 **ሐ.** 369

   ለ. 124 **መ.** 597

2. **ቀጥሎ ከቀረቡት ሙሉ ቁጥሮች መካከል በ4 እና በ5 ተካፋይ የሆነው የቱ ነው?**

   ሀ. 530 **ሐ.** 850

   ለ. 790 **መ.** 960

3. **ከሚከተሉት ውስጥ በተካፋይነት ደንብ መሰረት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?**

   ሀ. አንድ ሙሉ ቁጥር በ2 ተካፋይ ከሆነ በ6 ተካፋይ ይሆናል።

   ለ. በ9 ተካፋይ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች በ3 ተካፋይ ይሆናሉ።

   ሐ. በ8 ተካፋይ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች በ4 እና በ2 ተካፋይ ይሆናሉ።

   መ. አንድ ሙሉ ቁጥር በ3 እና በ4 ተካፋይ ከሆነ በ12 ተካፋይ ይሆናል።

4. **ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነው የቱ ነው?**

   ሀ. 169 የ13 አካፋይ ነው። **ሐ.** 340 የ40 ብዜት ነው።

   ለ. 0 የ100 አካፋይ ነው። **መ.** 210 የ14 ብዜት ነው።

@EtMathsNetwork

5. **ከሚከተሉት ውስጥ የ340 ብቸኛ ትንትን የሆነው የቱ ነው?**

   ሀ. $2 \times 5 \times 17$ **ሐ.** $2 \times 5^2 \times 17$

   ለ. $2^2 \times 5 \times 17$ **መ.** $2^2 \times 5^2 \times 17$

6. **ቀጥሎ ከቀረቡት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ12 ፣ 80 እና 96 ት.ጋ.አ (ትንሹ የጋራ አካፋይ) ስንት ነው?**

   ሀ. 1 **ሐ.** 4

   ለ. 3 **መ.** 6

7. **የ "ሀ" እና የ36 ት.ጋ.አ(ትንሹ የጋራ አካፋይ) 3 ነው። የሁለቱ ቁጥሮች ት.ጋ.ብ (ትንሹ የጋራ ብዜት) 468 ቢሆን የ "ሀ" ዋጋ ስንት ይሆናል?**

   ሀ. 1404 **ሐ.** 39

   ለ. 81 **መ.** 364

8. ሄለን በየ6 ቀኑ ትዋኛለች፣ በየ4 ቀኑ ትሮጣለች እና በየ16 ቀኑ ሳይክል ትነዳለች። ሶስቱን ተግባራት ዛሬ ካከናወነች በስንተኛው ቀን ሶስቱንም ተግባራት አንድ ላይ ታከናውናለች?

ሀ. 2 ሐ. 32

ለ. 24 መ. 48

9. $\frac{675}{720}$ በዝቀተኛ ሂሳባዊ ቃል ሲገለፅ ትክክል **የሆነው** የትኛው ነው?

ሀ. $\frac{15}{16}$ ሐ. $\frac{32}{41}$

ለ. $\frac{22}{23}$ መ. $\frac{13}{14}$

10. ከ $4\frac{11}{16}$ ጋር እኩል የሆነው አስርዮሽ ቁጥር የትኛው ነው?

ሀ. 4.5875 ሐ. 0.6875

ለ. 4.6875 መ. 0.5875

@EtMathsNetwork

11. ከ 0.067 ጋር እኩል የሆነው መቶኛ የትኛው ነው?

ሀ. 670% ሐ. 6.7%

ለ. 67% መ. 0.067%

12. $\frac{15}{4}$% በክፍልፋይ ሲገለፅ ስንት ይሆናል?

ሀ. $\frac{3}{80}$ ሐ. $\frac{15}{40}$

ለ. $\frac{3}{8}$ መ. $\frac{15}{4}$

13. ከሚከተሉት ውስጥ ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል የተቀመጠው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{3}{7}$ ⁞ 0.427 ⁞ $\frac{30}{7}$% ሐ. $\frac{3}{7}$ ⁞ $\frac{30}{7}$% ⁞ 0.427

ለ. 0.427 ⁞ $\frac{30}{7}$% ⁞ $\frac{3}{7}$ መ. $\frac{30}{7}$% ⁞ 0.427 ⁞ $\frac{3}{7}$

14. ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል **ያልሆነው** የትኛው ነው?

ሀ. $\frac{5}{8} > 6.25\%$ ሐ. $0.04 < \frac{2}{25}$

ለ. $67.3\% = 6.73$ መ. $12\ \frac{15}{16} \geq \frac{207}{16}$

15. አቤል በ1,250,000 ብር የገዛውን መኪና በ1,600,000 ብር ቢሸጥ የአቤል ትርፍ በመቶኛ ስንት ይሆናል?

ሀ. 0.28%　　ሐ. 28%

ለ. 0.72%　　መ. 72%

16. ሜሎስ ከቀረቡላት 25 ጥያቄዎች መካከል 80% ብታገኝ ምን ያህል ጥያቄዎችን በትክክል መለሰች?

ሀ. 20　　ሐ. 16

ለ. 18　　መ. 14

17. $5.08 + (2\frac{1}{5} - 2.2)$ ስንት ይሆናል?

ሀ. 2.2　　ሐ. 5.08

ለ. 4.09　　መ. 9.4

18. አንድ መስሪያ ቤት 123,000ብር ወርሀዊ ስራ ማስኬጃ ቢኖረው ለወረቀት መግዣ 29,000ብር፣ ለሰራተኞች አበል 7,650ብር እና ለመብራት ፍጆታ 10,500ብር ቢያወጣ መስሪያ ቤቱ በወሩ መጨረሻ ምን ያህል ብር ይቀረዋል?

@EtMathsNetwork

ሀ. 47,150ብር　　ሐ. 83,500ብር

ለ. 75,850ብር　　መ. 94,000ብር

19. የ $4\frac{3}{4}$ እና የ 3.2 ብዜት ስንት ነው?

ሀ. $\frac{608}{4}$　　ሐ. $\frac{12}{23}$

ለ. $\frac{95}{64}$　　መ. $\frac{76}{5}$

20. ሙገር የሲሚንቶ ፋብሪካ በሳምንት 330.5ቶን ሲሚንቶ ቢያመርት በ28 ቀን ምን ያህል ቶን ሲሚንቶ ያመርታል?

ሀ. 1322 ቶን　　ሐ. 1540 ቶን

ለ. 1416 ቶን　　መ. 1850 ቶን

21. $\frac{13}{5}$ በ0.6 ሲካፈል ድርሻው ስንት ይሆናል?

ሀ. $\frac{13}{3}$ ሐ. $\frac{23}{26}$

ለ. $\frac{39}{25}$ መ. $\frac{16}{5}$

22. የብርሀን ፍጥነት በሰዓት 1.08×10^9 ኪ.ሜ ነው። በመቁጠሪያ ቁጥር ሲገለፅ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 1,800,000,000 ሐ. 1,080,000,000

ለ. 108,000,000 መ. 108,000,000,000

23. $\frac{3}{4}$ሸ $= 24$ ይህን የእኩልነት ዓረፍተ ነገር እውነት የሚያደርግ የ "ሸ" ዋጋ ስንት ነው?

ሀ. 6 ሐ. 25

ለ. 18 መ. 32

24. ለያለእኩልነት ዓረፍተ ነገር $5ቀ + 7 > 47$ እውነት የሚያደርገው ቁጥር የቱ ነው?

ሀ. 6 ሐ. 8

@EtMathsNetwork

ለ. 7 መ. 9

25. ለያእኩልነት ዓርፍተ ነገር $40 - ጠ \leq 26$ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. $ጠ \leq 14$ ሐ. $ጠ < 14$

ለ. $ጠ \geq 14$ መ. $ጠ > 14$

26. $3በ < 7$ ለሚለው ያለእኩልነት ዓረፍተ ነገር በመቁጠሪያ ቁጥር ስብስብ ውስጥ የመፍትሄ ስብስብ የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. 1፣2 ሐ. 0፣1፣2

ለ. 1፣2፣3 መ. 0፣1፣2፣3

27. የሚከተለው ሰንጠረዥ ወተት በሊትር እና የወተት መሸጫ ዋጋ በብር ያሳያል፡፡ የመሸጫ ዋጋ ከሊትር ጋር በቀጥታ ይለዋወጣል፡፡

ሊትር(ሊ)	2	4	6
ብር(ብ)	100	200	300

ይህን ዝምድና የሚወክል ቀመር የቱ ነው?

ሀ. ብ = 100ሊ

ሐ. ብ = 50ሊ

ለ. ብ = $\frac{ሊ}{50}$

መ. ብ = $\frac{ሊ}{100}$

28. "በ" እና "ከ" ኢ-ቀጥተኛ ዝምድና አላቸው፡፡ በ = 3 እና መጣኝ ጠ = 18 ቢሆኑ የ "በ" እና "ከ" ጥንድ ቁጥሮች **ያልሆኑት** የትኞቹ ናቸው?

ሀ. (3፣6)

ሐ. (4፣4.5)

ለ. (7.5፣8)

መ. (9፣2)

29. ሰላም በዓመቱ መጀመሪያ 90,000ብር አላት፡፡ በየወሩ 6,500ብር ብታወጣ እና በዓመቱ መጨረሻ ላይ ከ25,000ብር ያላነሰ እንዲኖራት ብትፈልግ ለምን ያህል ወራት ማውጣት ትችላለች?

@EtMathsNetwork

ሀ. 10 ወራት

ሐ. 12 ወራት

ለ. 11 ወራት

መ. 13 ወራት

30. በሆስፒታል ውስጥ 10ታካሚዎች በ30 ቀናት ውስጥ 300ሊትር ወተት ይጠቀማሉ፡፡ በተመሳሳይ መጠን በ5 ቀናት ውስጥ ስንት ታካሚዎች 100 ሊትር ወተት ይጠቀማሉ?

ሀ. 10 ታካሚዎች

ሐ. 30 ታካሚዎች

ለ. 20 ታካሚዎች

መ. 40 ታካሚዎች